የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 5
ADDIS ABABA 17th November, 2005

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፭/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታን ከምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ ለማጥፋት ለተነደፈው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………. ገጽ ፫ሺ፫፻፲፩

CONTENTS

Proclamation No. 475/2005

African Development Fund Loan Agreement for Financing the Creation of Sustainable Tsetse and Trypanosomiasis Free Areas in East and West Africa Project Ratification Proclamation………. Page 3311

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፭/፲፱፻፺፰

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታን ከምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ ለማጥፋት ለተነደፈው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፱ሚሊዮን፭፻፶ሺ ዩኒትስ ኦፍ ካውንት /ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሃምሳ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ ካውንት/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታን ከምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ ለማጥፋት ለተነደፈው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፭/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 475/2005.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLLIC OF ETHIOPIA AND THE AVRICAN DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS,** a Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of nine million five hundred fifty thousand units of Account (UA 9,550,000) for financing the Creation of Sustainable Tsetse and Trypanosomiasis Free Areas in East and West Africa Project;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 13th day of October, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for Financing the Creation of Sustainable Tsetse and Trypanosomiasis Free Areas in East and West Africa Project Ratification Proclamation No.475/2005."

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፮ ቀን ፪ሺ፭ የተፈረመው ቁጥር 2100150009198 የብድር ስምምነት ፀድቋል።

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፱ሚሊዮን፭፻፶ሺ ዩኒትስ ኦፍ ካውንት /ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሃምሳ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ ካውንት/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement No. 2100150009198 signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Africa Development Fund on the 16th day of May, 2005 is ratified;

**3. power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of nine million five hundred fifty thousand United of Account (UA 9,550,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

The Proclamation shall enter into force on 17th day of November , 2005.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of November, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት